# በዳላስ ቴክሳስ ከ 2.5 ሚሊዮን ብር በላይ
# ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ተሰበሰበ

በጂቲፒ ዳላስ ኮሚቴ ለህዳሴው ግድብ ግንባታ ድጋፍ ለማሰባሰብ ሕዳር 3-ቀን 2004 ዓ/ም በ ኢንተር ኮንትኔንታል ሆቴል በተካሄደው ዝግጅት በቦንድ ሽያጭ እና ስጦታ ከ 2.5 ሚሊዮን ብር በላይ ለመሰብሰብ ተችሏል።

በዕለቱ በክብር እንግድነት በአሜሪካን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ልዩ መልእክተኛ እና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር የተከበሩ አምባሳደር አቶ ግርማ ብሩ እና የተከበሩ አምባሳደር አቶ ሙሌ ታረቀኝ ተገኝተዋል።

ክቡር ልዩ መልእክተኛ እና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር አቶ ግርማ ብሩ በአገራችን እየተከናወነ ያለው ከፍተኛ የኤኮኖሚ ዕድገት ከተጠበቀው በለይ ማደጉን አብራርተው ባንጻሩም ተመሳሳይ የሆነ የሀይል ፍላጎት መከሰቱን ተናግረው ይህንንም ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል የሀይል አቅርቦት እንዲኖር መንግሥት ስላወጣቸው ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች በሰፊው ገለጻ አድርገዋል።

ክቡር አምባሳደር አቶ ሙሌ ታረቀኝ በበኩላቸው በውጭ የሚገኙ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላት በትውልድ አገራቸው እየተካሄደ በሚገኘው የሰላም፣ የልማት፣ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ሥርአት ግንባታ ሂደት ላይ በመሳተፍ ድርሻቸውን እንዲወጡ ሲያሳስቡ ለፖሊሲው መሳካት ገንቢ ሀሳቦችን ለማግኘት ስላለው እንቅስቃሴ በሰፊው አብራርተዋል።

የአገራችን ከተመፅዋችነት ማላቀቂያ መንገድ አንዱ፣ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን በተሟላ ሁኔታ ማሳካት ነው

የታላቁ የሕዳሴ ግድብ ለአገራችን ልማት ቀጣይነት ማረጋገጫ ታላቅ ድርሻ አለው

የዳላስ ቴክሳስ ጂቲፒ አስተባባሪ ኮሚቴ